# የመንጃ ፈቃድዎን መልሰው ለማግኘት እርዳታ ያስፈልግዎታል ወይ?

የኖርዝዌስት የፍትህ ፕሮጀክት (Northwest Justice Project) በ Washington ውስጥ ጠበቃ የመቅጠር አቅም ለሌላቸው ሰዎች፣ በነጻ የሲቪላዊ (የወንጀል-ያልሆነ) ሕጋዊ አገልግሎቶችን ይሰጣል። መስራት እንዲችሉ የመንጃ ፈቃድዎ የሚያስፈልግዎ ከሆነና፣ የመንጃ ፈቃድዎ የተገደብዎ ከነዚህ በታች ካሉት ምክንያቶች ውስጥ፣ በአንዱ ከሆነ፣ ልንረዳዎ እንችላለን፤

- ያልተከፈሉ የትራፊክ መቀጮዎች
- ያለ መድን ዋስትና ሲነዱ ባጋጠምዎ የመኪና አደጋ ምክንያት መታገድ
- በታገደ መንጃ ፈቃድ በመንዳትዎ ምክንያት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ፍርድ ተበይኖብዎት ከሆነና፣ የእገዳ ጊዜው አብቅቶ ቢሆንም፣ ያልተከፈለ መቀጮ ካለብዎት

እኛ ልንረዳዎ የምንችለው፣ ፍርድ ቤቱ ባለብዎ የትራፊክ ትኬት ላይ ፍርዱን በይኖ ከሆነ ብቻ ነው። ፍርድ ቤት እርስዎ በፍርድ ቤቱ ባይገኙም እንኳን፣ ፍርድ ሊያስተላልፍ ይችላል። ለእርዳታ ብቁ እንደሆኑ ለማወቅ፣ በነጻ ወደ ሚያስደውለው የስልክ ቁጥር ከ 9:10 a.m. - 12:25 p.m. ድረስ በ **(888) 201-1014** ይደውሉ።

**የልጅ ማሳደግየ እርዳታ (ቻይልድ ሳፖርት) ባለመክፈል ወይም እንደ ሰክሮ መንዳት (DUI) የመሳሰሉ፣ በአንዳንድ የትራፊክ የወንጀል ፍርዶች ምክንያት የመንጃ ፈቃድ ከታገደ፣ በዚያ ላይ እርዳታ መስጠት እንደማንችል ይወቁ።**

## የ Northwest Justice Project ምንድነው?

የ Northwest Justice Project (NJP)፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች፣ በነጻ ሲቪላዊ የሕጋዊ አገልግሎቶችን የሚሰጥ፣ በ Washington State ውስጥ 13 ቢሮዎች ያሉት ያለት ትርፍ የሚንቀሳቀስ ስቴይት-አቀፍ ድርጅት ነው።

የ NJP ተልእኮ፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ደንበኞች፣ በቀጥታ ወይም ቀልጣፋና እንደሚሰሩ በተረጋገጠላቸው ሪፈራሎች በኩል፣ በሚከሰቱ ከፍተኛ እልባትን ማግኘት ባለባቸው ችግሮች ላይ፣ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውንና ነጻ የሆኑ ሕጋዊ አገልግሎቶችን መስጠት ነው።

THE ALLIANCE for Equal Justice MEMBER

NJP

LSC